የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ — የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd year No. 10
ADDIS ABABA - 15th February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፹፰ ዓ·ም·
የማዕድን (ማሻሻያ) አዋጅ ..................................... ገጽ ፻፲፯
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፰ ዓ·ም
የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ..................................... ገጽ ፻፲፰

## CONTENTS

Proclamation No. 22/1996
Mining (Amendment) Proclamation .......... Page 117
Council of Ministers Regulations No. 2/1996
Customs Tariffs Council of Ministers (Amendment) Regulations ................................................ Page 118

## አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፹፰
## የማዕድን አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የማዕድን ሀብት ልማትን ለማስፋፋት የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማዕድን (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የማዕድን አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· በአንቀጽ ፵፬ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ውስጥ "እስከ አሥር በመቶ (፲ ፐርሰንት) የሚደርስ አክሲዮን ያለምንም ክፍያ ሊይዝ ይችላል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ሁለት በመቶ (፪ ፐርሰንት) አክሲዮን ያለምንም ክፍያ ይይዛል" በሚል ተተክቷል ።

፪· የአንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል ፤

## PROCLAMATION NO. 22/1996
## A PROCLAMATION TO AMEND THE MINING PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Mining Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Mining (Amendment) Proclamation No. 22/1996."

2. *Amendment*

The Mining Proclamation No. 52/1993 is hereby amended as follows:

1) The clause "may acquire without cost a participation interest of up to ten percent" in the first sentence of Article 44 is hereby deleted and replaced by the clause "shall acquire without cost a participation interest of two percent."

2) Sub-Article (1) of Article 46 is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article (1):

"፩/ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራዎችና በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ፤ ሌሎች ማናቸውንም የማዕድን ሥራዎችን በተመለከተ የፍለጋና የምርመራ ፈቃድ ከሆነ ሚኒስቴሩ ፣ ጣምራ ፈቃድና የማዕድን ማምረት ፈቃድ ሲሆን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያጸድቀው ደንብ መሠረት ሚኒስቴሩ ፣ ይሰጣል ።"

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

"(1) The power to issue artisanal mining license and construction minerals mining license undertaken by domestic investors is vested in the Mines and Energy Bureau of National/Regional Self–Governments; while prospecting, exploration and mining licenses for all other mining operations shall be issued by the Ministry, subject to regulations approved by the Council of Ministers in respect of combined and mining licenses."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 15th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

---

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፰
## የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በዓለም አቀፍ የተዋሀደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ማሻሻያ</u>

ከጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፲፱፻፹፭ ጋር ተያይዞ የሚገኘው የጉምሩክ የዕቃ ቀረጥ ሥርዓትና ተመን ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ተሻሽሏል ።

፫· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥር ፩ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 2/1996
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE CUSTOMS TARIFFS REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 4 of the International Convention on the Harmonized Commodity Description and Coding System Ratification Proclamation No. 67/1993.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Customs Tariffs Council of Ministers (Amendment) Regulations No. 2/ 1996."

2. *Amendment*

The Customs Tariffs Classification System of Goods and Rates attached to the Customs Tariffs Regulations No. 122/1993 is hereby amended by the schedule attached hereto.

3. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force as of the 10th day of January, 1996.

Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 1996.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE